# ወፌ,ያሬድ

ከ ፍቅሬ ቶሎሣ (ዶ/ር)

*ወፌ,ያሬድ፥ ወፌ,ያሬድ፥ ወፌ,ያሬድ፥ አንች የኔ ገድ፥*
*የኔ ሲሳይ፥ የኔ ነሲብ፥ የተባረክሽ ከወፍ ነገድ፥*
*አዝኛለሁ ዘምሪልኝ፤*
*ዛሬ ዕድሌን አስምሪልኝ።*
*ሰልችቶኛል የሰው ሮሮ፥*
*ዜማ 'ርጠቢኝ ካንች ጉሮሮ፥*
*አንችን ናፍቋል የኔ ጆሮ፥ ወዳጄ ሆይ ድምፅሽ አምሮ።*
*ማሕሌትሽ ለነፍሤ መድህን፥ ዜማሽ ፈውሤ ለኔ አእምሮ።*

*የተፈጠርሽ ለመዘመር፥*
*ዜማ ብቻ ለመቀመር፥*
*ለሰው ሀሤት ለመጨመር።*
*ሽር አታቂ ማዜም 'ንጂ፥ ማሕሌታት ስታወርጂ፥*
*ወይን መዝሙር ስትቀጂ፥ በክፉው በደጉ ሳትፈርጂ፥*
*እንደ ፀሃይ ለሁሉ ስታበሪ፥ ሰውን ልፈርጅ ብለሽ ሳትፈርጂ፥*
*ያለአድልኦ ለሁሉ ስትዘምሪ፥ ልስልስ ሆነኮ ደረቅ ድንጋይ፥*
*ብራ ሆነኮ ርጥብ ሰማይ፥ ለመለመኮ እሳት ሀጋይ፥*
*ሩህሩህ ሆነ'ኮ የጨካኝ ልብ፥*
*ሰክኖ አደበኮ ቅልብልብ።*

*ዘምሪልኝ ገጣሚዬ፥*
*ሬት ህይወትን አጣሚዬ፥*
*አስተ,ጋቢ ካምባ አምባ፥*
*ይደርቅ ዘንድ የኔ እምባ።*

*ከመስዕ ብቅ አልሽ ወይስ ከናጌብ፥*
*ከዱዳሌብ ብቅ አልሽ ወይስ ከአዜብ?*
*ወይስ አንችዬ ተመዘዝሽ ከሩቅ ኮሬብ፥*
*ወጣሽ ወይ ልበል ከሃኖስ፥*
*ወይስ ከሰማየ ውቅያኖስ፥*
*መዝሙር ልታበሪ እንደፋኖስ?*
*በድቅድቅ ፅልመት ሆነሽ ወርቀ-ጨረር፥*
*ከራማ ፈለስሽ ወይስ ከኤረር?*
*ከፅርሃአርያም ወይስ ከዒዮር፥ ቅላጼሽን በመቀያየር፥*
*እሪታንና ዋይታን አዳፍነሽ በዜማሽ ልታጣፍጭ አየር?*
*ከየት ተገኘሽሳ አንች አዝማሪ?*
*የህልውና ቅመም፥ የህይወት አሳማሪ።*

*ወፌ,ያሬድ፥ ወፌ,ያሬድ፥ ወፌ,ያሬድ፥ አንች የኔ ገድ፥*
*የኔ ሲሳይ፥ የኔ ነሲብ፥ የኔ እጣፈንታ፥ ምሩፅ ከወፍ ነገድ፥*
*ተቋዳሽ በባህሪሽ የኔን ዐርባ ቀን እድል፥ አንቺ መዝሙር-ሰገድ፤*
*ምንም እንዳንችም ባልዘምር በመንቆሬ፥*
*አዜማለሁኮ በብዕሬ፥ ለሕይወት በመቆርቆሬ።*
*የኔም ያደርቃል፥ያንች እምባ እንደሚያደርቅ የሌሎች እምባ፥*
*እምባዬ በየሰዉ ቤት እየገባ፥ መዝሙሬ አስተ,ጋብቶ ካምባ አምባ።*

ምንም እንዳንችም ባይጥም መዝሙሬ፥ ሲበዛ ጻዕሬ
አዎን እህቴ ሆይ! እኔም እዘምራለሁኮ በብእሬ።

ዕጣ ፈንታዬን አስምሪልኝ፥
እቴሸንኮሬ፥ እልሻለሁ ዘምሪልኝ፤
ባዘን ምትክ ፍሥሃ አፍሪልኝ!
ልቤን በፍንጥዝ አስጨፍሪልኝ፤
ከፍቶኝ ባለም ግፍ፥ ተንኮል፥
እይው እምባዬ በጉንጨ ሲኮለኮል!
እዪውማ ቆዝሜ፥ እዪው ሆድ ብሶኝ በሰው ጭካኔ፥
የሃራ-ሰማይን ሃዝን ተሸክሜ፥ ሃዘን ለመሸከም በመካኔ!
እንዲበጠስ የብካዬ ሥር፥ እንዲነቀል የሃዘኔ ሥራይ፥
አንቺዬ ዘምሪልኝ በዕዝል፥ አንቺዬ አንጎራጉሪልኝ በአራራይ!

የሆድሽን ማን አውቆልሽ ሆዴ፥ ዳሩ ለቅሶሽ ይሆን ያንቺ ዜማሽ
ደስታሽ መስሎኝ የምሰማሽ?... ዋይ!.. ይሆን እንዴ የፍጻሜ ዋዜማሽ?
ያሬድን አክለሽ በባሕሪሽ፥ ጸሎት ሆኖ አንጣሪሽ፥ ምህላ ሆኖ አጣሪሽ፥
አንቺዬ፥ ውድዬ፥ ያባሽውን ግለጭልኝ፥ ውዳሴ ማቅረብሽ ይሆን ለፈጣሪሽ?
ሃዘንሽም ከሆነ ያንቺ መዝሙር፥
ለኔ ሃሴት ነው፥ ለነፍሴ ስሙር!

ማሕለታዊው ያንች ቅድማያት፥
ቅዱስ ያሬድ ላከሽ ከሰማያት?
ዘምሪለት ለፍቅሬ አዝኗል ብሎ፥
ሃሴት ከሱ ርቆ፥ ኮብሎ ፥
የዜማ እምባሽ ልቤን ባሴት እንዲያጥብ፥
ቆዛሚ መንፈሴን ከሃዘን እንዲያናጥብ።
ላከሽ ወይ ጻድቁ ማሕሌታዊ፥ በከሃሊው አምላኩ ቸርነት
የሆነው ዘላለማዊ፥ መዝሙርሽ ነፍሴን እንዲያወጣት ሀርነት?

ለኔ ስትይ አዝሚልኝ፤
ለኔ ስትይ ቆዝሚልኝ፤
አዝኛለሁ ወፊያሬድ፥ እባክሽን ዘምሪልኝ፤
ፈውሤ አንቺ ነሽ ወፊያሬድ፥ ዛሬ ገዴን አስምሪልኝ።

ወፊያሬድ፥ ወፊያሬድ፥ ወፊያሬድ፥ አንች የኔ ገድ፥
የኔ ነሲብ፥ የኔ ዕድል፥ ቅድስት አንቺ ከወፍ ነገድ።
ዜማ ወንዝሽ፥ ማህሌት ቀላይሽ፥ መዝሙር-ሰገድ።
እይውማ መንፈሤ ሲያምጽ፥
ሰልችቶት ሻካራ ድምጽ።
እሰየው! እንደሱ ቅላጼሽ በሕዋ ይሥረቅረቅ፥
እፈቅድልሻለሁ አንችዬ፥ ልሳንሽ የኔን ልብ ይሥረቅ፥
ቀልቤ ባንደበትሽ ይመረቅ፥
አንጀቴ ይራስ በማሕለትሽ መረቅ።

ዝንታለም ስትዘምሪ አይሰበር ቅስምሽ፥
ኧረ ከያሬድ በፊት ማን ነበረ ስምሽ?
ጥንት ማሕሌት ስታወርጂ በኡኡታ ላይ እያደምሽ፥
አንች አልነበርሽም እንዴ ቅዱስ ያሬድን የቀደምሽ?

ያንችም የያሬድም እስትንፋስ መንፈስ ስለሚያረግ ሥክር፥
በሱ ስም መጠራትሽ ላንቺም ለሱም ነው ሕያው ምሥክር።
አንቺ ብትቀድሚውም በጀማሪነት፥
ያሬድ ተወዳዳሪሽ ነው በዘማሪነት።

ጉሮሮሽ እጹብ ዜማ እንዲያፈልቅ ድምጸ-ኅብርን አቀነባብሮ፥
እስቲ አድራሻሽን ንገሪኝ፥ ከየት ተገኘሽ ብርቅዬዋ ሽንብሮ?
ከ "ህመልማል" ነሽ ወይስ ከኛው ምድር፥
ከሌላ ያልመጣሽ ለውድድር?
ወይስ ከ "ረሃም" ብቅ አልሽ ከ ዓለመ ብልሃን፥
እንደኔ ልቡ ለጨለመበት ልትሆኚለት ብርሃን?
ከ " ገውዛ" ዓለም መጣሽ ወይ "አልቅምም" ብለሽ "አፈር"
"መዝሙር ላመነጭ እንጅ አልተፈጠርኩም አፈር ለመፈርፈር።"

ከ "ሽርታ" ዓለም አፈተለክሽ ልበል ወይ፥
መበላላታቸው አሰኝቶሽ " አወይ! "
እኔ ልደንግጥልሽ፥ ደንግጠሽ ከ "ሰውድ" ዓለም ሸሽሽ 'ንዴ፥
እሳታዊዎቹ ፍጡራን፥ ዐይተሽ ተፈጥሮን ሲያጋዩት ባንዴ?
ከ "ሰንበላ" ዓለም ተሥፈንጥረሽ አይደንቅም ብትዘልቂ፥
አእዋፍ ርሥበርሡ ሲፋጅ አንቺም አብረሽ እንዳታልቂ።

እግዜርን ከሚያፈቅሩት፥ ያምርብሻል ብትፈልሺ ከ "ሚሳን" ዓለም፥
አምላኩን አውቆ ካንቺ እኩል፥ እንደነሱ ለፈጣሪ የሚዘምር የለም።
አምናለሁ ከ "አቅራብ" ከውሃውስ ዓለም እንዳይደለሽ፥
እንደ ዳክዬ ከውሃ አጣብቆ ፈጣሪሽ ስላልበደለሽ።
ከ "ቀውሳ" ከ እሳቱ ዓለምም አይደለሽ፥ ተፈጥረሽ ከ 'ሳት፥
በልተሽ እሳት፥ የምትጠፊ በ 'ሳት፥ አእምሮሽን በመሳት።

ከ "ዠዲ" ዓለም ትሆኚ አንቺዬ፥ ከጠቢባኑ ሃገር?
በመንኮራኩር ሃራሰማዩን፥ ከሚያርሱት ያለመቸገር?
ከ "ደለዋ" ዓለምስ አትሆኚም ከዛ ከባርባሮሱ ፅልመት፥
ትእልፌተ-አእላፋቱ በጭለማ ከሚድሁበት ካመት ዓመት።
"ሁት" ከተባለው ዓለምም ትከንፊያለሽ አልልም፥
እናትሽ ከሞተች አብረሻት ሞተሽ ስለምትዪ እልም።
ይመስለኛል ከ "ኢየሩያ" ነሽ ከ ሕያውያኑ ዓለም፥
ወይም ከ "አርያም" ነሽ የተላክሽ እኔን ለመሸለም።

ከ የትም ከች! አልሽ ከየትም፥ ወፈያሬድ ነሽ የኔ ስጦታ፥
ጣፋጭ አፍሽን ከፍተሽልኝ ይሟላ፥ ይገኝ የልቤ እጦታ።
በዜማሽ ክንፍ ተንሳፍፌ፥ ልሽሽ ከ 'ዚህ ዓለም ቱማታ፥
አቀንቅኚልኝ በጽባህ፥ ዘምሪልኝ በቀትር፥ አዝሚልኝ በማታ።
ተስረቅረቂልኝ በአየሩ፥ አንቺዬ ንዘሪልኝ ጠፈሩ ላይ፥
በጆሮዬ እንድመጥቅ ከሰማየሰማይ፥ በዐይኔ ጉድፍ ሳላይ።

ትመጫለሽ አሉ በምሥጢር ደርሰሽ ከኤ ዶም ገነት
በትካዝ አረፍ ብለሽ ከፈራረሰው ያዳምና ሔ ዋን ሠገነት።
ዋይ!ዋይ! ብለሽ እየቆዘምሽ፥ ተጸፅተሽ በወደመው፥ ተሞልተሽ በትዝታ፥
ወላጆቻችን በጥፋት ያጡትን ተድላ እያየሽ፥ በመሪር ሰመመን ድንግዝግዝታ።

እስቲ አጫውችኝ አንችዬ፥ እውነት
እንደ ድሮው አሁንም ያምራል ገነት?

ወፈያሬድ፥ ወፈያሬድ፥ ወፈያሬድ፥ አንች የኔ ገድ፥
የኔ ሲሳይ፥ የኔ ነሲብ፥ የኔ እድል፥ ምሩፅ ከወፍ ነገድ፥
ዜማ ወንዝሽ፥ ማህሌት ቀላይሽ፥ መዝሙር-ሰገድ።
ዕጣ ፈንታዬን አስምሪልኝ፥
እቴሽንኮሬ፥ እልሻለሁ ዘምሪልኝ፤
ባዘን ምትክ ፍሥሃ አፍሪልኝ!
ልቤን በፍንጥዝ አስጨፍሪልኝ፤
ከፍቶኝ ባለም ግፍ፥ ተንኮል፥
እይው እምባዬ በጉንጬ ሲኮለኮል!
እዩውማ ቆዝሜ፥ እዩው ሆድ ብሶኝ በሰው ጭካኔ፥
የሃራ-ሰማይን ሃዝን ተሸክሜ፥ ሃዘን ለመሸከም በመካኔ!
እንዲበጠስ የብካዬ ሥር፥ እንዲነቀል የሃዘኔ ሥራይ፥
አንቺዬ ዘምሪልኝ በዕዝል፥ አንቺዬ አንጎራጉሪልኝ በአራራይ!

ከዙፋኔ ወርጄ ለክብርሽ፥
ዘውዴን ከራሴ አውርጄ ለመዝሙርሽ፥
ሱባኤ ገብቼልሽ ቆሜ በባዶ እግሬ፥ ሰውቼልሽ አዝማኔን፥
ዝንታለም ባደምጥሽ አትሰለችኝ፥ እንድትመርቂው እርግማኔን።
ቋቅ! ብሎኝ የዓለም ንትርክ፥ አንገሽግሾኛል የሰብዕ ንዝንዝ፥
ያጸድቅሻል፥ ነፍስ ዝርቢኝ የናቴ ልጅ፥ ሞቼ ነኝና ግንዝ።

ዳሩ ለኔ ብቻ ማ ዳረገሽ? የሰውን ልብ ሁሉ እየማስሽ፥
በማሕሌትሽ አስፈንጥዥያቸው፥ በኔ አይገታ አድማስሽ።
በኔ አይታገድ አጽናፍሽ፥
ብረሪባቸውማ ባክናፍሽ!
ዘምሪ ላለም በወርቅ አፍሽ፥
እዩ ዓለም ሲሰቃይ፥ በሰቆቃ ሲያነባ፥
ዘምሪለት ለሰውልጅ ሁሳ ፥ የፈረሰ ልቡ እንዲገነባ።

ንገሽበት በሰማዩ አንደ መንኮራኩር፥ እንደ ጠፈር-መርከብ፥
ዜማሽ ሕዋውን ሠንጥቆ፥ ለካልኢት ይብለጭለጭ እንደበራሪ ኮከብ።
ምን ቦጣሽ እኔጋ ብቻ፥
ከኔ ያለሽ ይመስል ጋብቻ?
ተወልደሻል ለነጻነት፥
ተፈጥረሻል ለሀርነት፥
ገስግሽና ወዳጄ አበረታቺ፥ አነቃቂ ቀልቡ የባዘነውን፥
ንጎጂና ባልንጀሬ፥ አጽናኚው እንደኔ ያዘነውን።
ተቀምመሽ ለሰው ልጅ ልብ እነጻ፥
ብረሪ ወዳሻሽበት ጓዴ፥ አንቺ ነሽና ነጻ!
ፏልሊበት በሰማዩ፥ ቧርቂበት በጠፈሩ፥ ቱር! ብለሽ ተነጠቂ፥
የድምፅ፥ የዜማ ጸዳል ሆነሽ፥ አካልዬ በዓለም ልትፈነጠቂ።

ፍጡራንን ሁሉ ለማጽናናት ነውና የተሠራሽ፥
ማንም ለኔ ብቻ ሊልሽ አይችል፥ አዎ ለሁሉ ነሽ ደራሽ።
እንደ ሌላው ወፍ ሁሉ አንቄ ላስርሽ ከ እትት፥
አልችልም፥ አይገባኝምም ጭራሽን ይዤ ልጎትት።

ሁር ነሽ፥ ነጻ ነሽ፥ በይ ብረሪ! በግርማ ሞገስሽ ክበሪ!
በዜማሽ ጸዳል አንቺዬ፥ ጭለማውን ዓለም እንድታበሪ!

ለጊዜው ግን፥ወፊያሬድ፥ ወፊያሬድ፥ አንች የኔ ገድ፥
የኔ ሲሳይ፥ የኔ ነሲብ፥ የኔ እድል፥ ምሩፅ ከወፍ ነገድ፥
ዜማ ወንዝሽ፥ ማህሌት ቀላይሽ፥ መዝሙር-ሰገድ፡፡
ዕጣ ፈንታዬን አስምሪልኝ፥
እቴሸንኮሬ፥ እልሻለሁ ዘምሪልኝ፤
ባዘን ምትክ ፍሥሃ አፍሪልኝ!
ልቤን በፍንጥዝ አስጨፍሪልኝ፤
ከፍቶኝ ባለም ግፍ፥ ተንኮል፥
እይው እምባዬ በጉንጩ ሲኮለኮል!
እዪውማ ቆዝሜ፥ እዪው ሆድ ብሶኝ በሰው ጭካኔ፥
የሃራ-ሰማይን ሃዝን ተሸክሜ፥ ሃዘን ለመሸከም በመካኔ!
እንዲበጠስ የብካዬ ሥር፥ እንዲነቀል የሃዘኔ ሥራይ፥
አንቺዬ ዘምሪልኝ በዕዝል፥ አንቺዬ አንጎራጉሪልኝ በአራራይ!

(እንደ ፈረንጅ አቆጣጠር ሰኔ 27 ቀን 2008)

ውድ አንባቢ ሆይ! ግጥም መጻፍ የጀመርኩት በ 12 ዓመቴ ነበር፡፡ እስከ 23 ዕድሜዬ ድረስ የተለያዩ የግጥም ቅርጾችን ስሞክር ቆየሁ፡፡ ቤት ሳልመታ የምገጥምበትም ጊዜ ነበር፡፡ በመጨረሻ ግን ልዩ የቤት አመታትን አዳበርኩ፡ እሱውም እንደ ከበሮ ለመምታት መጣጣር ነው፡፡ ሥራዬ ብዬ፥ አማርኛ ቋንቋ እስከ ሚፈቅድልኝ ድረስ፥ ቢቻል በሶስት ተከታታይ ፊደሎች፥ ካልተቻለ በሁለት፥ እለዛም በ አንድ ጠንካራ ፊደል ለመግጠም እሞክራለሁ፡፡ እላይ የሰፈረው ግጥም በዚህ ስልት የተጻፈ ነው፡፡ ለምሳሌ –

“ ተነጠቂ ” ን በ “ልትፈነጠቂ” “እየማስሽ ” ን በ “ አድማስሽ ” “ጋ ብቻ ” ን በ “ ጋብቻ ” “ ገድ ” ን በ “ ነገድ ” “አፍሪልኝ ” ን በ “ አስጨፍሪልኝ ” ”ቅድማያት ” ን በ “ ሰማያት ” “ሥክር “ ን በ “ ምሥክር ” ገጥሜአለሁ፡፡ ያለፉትም ሆኑ የአሁኖቹ የኢትዮጵያ ገጣምያን እንደዚህ ገጥመው አንብቤ አላውቅም፡፡ ሥለዚህ፥ ለጊዜው ይህ የኔ የአገጣጠም ዘይቤ ወይም ስልት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ፥ ግጥምን የሚያጠኑ ሊቃውንት ለወደፊቱ የኔን ግሞች በሚተነትኑ ጊዜ ይህን ሐቅ ያጤኑታል፡፡

ፍ/ቶ